International
Labour
Organization




# በውጭ አገር ስራ ስምሪት ላይ የሚሰሩ
# የባለድርሻ አካላት መብትና ግዴታ

Copyright © International Labour Organization 2020
First published 2020

Publications of the International Labour Office enjoy copyright under Protocol 2 of the Universal Copyright Convention. Nevertheless, short excerpts from them may be reproduced without authorization, on condition that the source is indicated. For rights of reproduction or translation, application should be made to ILO Publishing (Rights and Licensing), International Labour Office, CH-1211 Geneva 22, Switzerland, or by email: rights@ilo.org. The International Labour Office welcomes such applications.

---

Libraries, institutions and other users registered with a reproduction rights organization may make copies in accordance with the licenses issued to them for this purpose. Visit www.ifrro.org to find the reproduction rights organization in your country.

---

ISBN 9789220320723 (print)
ISBN 9789220320730 (Web pdf)

**Also available in** [English]: Rights and Responsibilities of Relevant Actors on Labour Migration in Ethiopia, ISBN 978-92-2-031988-8 [print] ISBN 978-92-2-031987-1 [web pdf].

---

The designations employed in ILO publications, which are in conformity with United Nations practice, and the presentation of material therein do not imply the expression of any opinion whatsoever on the part of the International Labour Office concerning the legal status of any country, area or territory or of its authorities, or concerning the delimitation of its frontiers.

The responsibility for opinions expressed in signed articles, studies and other contributions rests solely with their authors, and publication does not constitute an endorsement by the International Labour Office of the opinions expressed in them.

Reference to names of firms and commercial products and processes does not imply their endorsement by the International Labour Office, and any failure to mention a particular firm, commercial product or process is not a sign of disapproval.

Information on ILO publications and digital products can be found at: www.ilo.org/publns.

---

Printed in Ethiopia

# በውጭ አገር ስራ ስምሪት ላይ የሚሰሩ የባለድርሻ አካላት መብትና ግዴታ

በዚህ በራሪ ፅሑፍ ውስጥ የተገለፀው መረጃ የተዘጋጀው በመካከለኛው ምሥራቅ አረብ አገራት በቤት ወስጥ ሠራተኝነት የተሰማሩ ኢትዮጵያውያንን የተመለከቱ ሥራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ የሚመለከታቸው አካላትን መብትና ግዴታዎች የተመለከቱ አጠቃላይ መረጃዎች ሲሆን መነሻውም ነባራዊ መረጃዎችና የሕግ ማዕቀፎች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ የተገለፁት ማጣቀሻዎች ዓላማ ለመረጃነት እንዲያገለግሉ ብቻ ሲሆን የትኛውንም ድርጅት የማይወክሉና ከየትኛውም ድርጅት የተላለፉ አይደሉም፡፡

ከዚህ በታች የተገለፀው መረጃ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008ን[1]፣ እ.አ.አ በ2012 የኢትዮጵያ መንግስት ከካታር እና ጆርዳን፣ በ2017 ከሣዑዲ አረቢያ፣ በ2018 ከተባበሩት አረብ ኢመሬቶች (የተ.አ.ኢ) መንግስት ጋር የተፈራረመችውን የሁለትዮሽ የሥራ ስምሪት ስምምነትን፣ እንዲሁም ሣዑዲ አረቢያ የቤት ውሰጥ ሠራተኞችን አስመልክቶ ያወጣችው ውሳኔ 310/1334 (እ.አ.አ በ2013)፣ የካታር የቤት ውስጥ ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 13/2018፣ የተባበሩት አረብ ኢመሬቶች ፌደራል አዋጅ ቁጥር 10/2017 የድጋፍ አገልግሎት ሰጪ (የቤት ውስጥ ሠራተኞች አዋጅ) እና የጆርዳን የቤት ውስጥ ሠራተኞች፣ አብሳዮች፣ አትክልተኞች እና ተመሳሳይ የሥራ ክፍሎች ደንብ ቁጥር 90/2009ን መሰረት በማድረግ ነው[2]፡፡

[1] https://chilot.me/wp-content/uploads/2017/04/proclamation-no-923-2016-ethiopia_s-overseas-employment-proclamation.pdf

[2] https://www.ilo.org/dyn/travail/docs/642/Regulation%2090.2009.pdf



# 1. በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ የቤት ውስጥ ሠራተኞች መብት እና ግዴታ

## በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ የቤት ውስጥ ሠራተኞች መብት ፤

በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ የቤት ውስጥ ሠራተኞች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፣

### ከጉዞ በፊት ኢትዮጵያ እያሉ

- ለሥራ በሚሰማሩበት ሙያ መሰልጠንና እራሳችሁን በአስፈላጊው ሙያና ዕውቀት ብቁ ማድረግና ስለ ውጭ አገር ሥራ ሥምሪት መረጃ ማግኘት፣
- ስለ ሥራ ሁኔታውና ቅጥሩ ትክክለኛ፣ ግልፅና የጠራ፣ በቀላሉ መረዳት በሚችሉበት ሁኔታ ግንዛቤ ማግኘት፣ እንዲሁም የአሠሪውን አድራሻና ስም፣ የሥራ ቦታ፣ የኮንትራት ጊዜ፣ የሥራውን ዓይነትና የሥራ ሁኔታ፣ ደመወዝና የመክፈያ ጊዜ፣ የቀን የሥራ ሰዓት፣ የዓመት ዕረፍት፣ የሣምንትና የቀን የዕረፍት ጊዜ፣ ወደ አገር ቤት የመመለሻ መስፈርቶችን፣ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የተቀመጡ መስፈርቶችና ተዛማጅ ሁኔታዎችን መረዳት፣

- በአገርዎ ሆነ በመድረሻ አገር የባንክ ሒሳብ ደብተር በመክፈት ደመወዝዎን ወደ አገር ቤት በባንክ ወይም በሌላ ሕጋዊ በሆነ ዘዴ መላክ፤
- የሥራ ውሉን ሙሉ በሙሉ ከተረዱና በይዘቱ ከተስማሙ በኋላ ከአሠሪው ወይም ከኤጀንሲው ጋር መፈረም፤

## በተቀባይ አገር ሲደርሱና ወደ ሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ፣

- ከግዳጅ ሥራ ነፃ መሆን፣
- አድልዎ በሌለበት ሁኔታ (የፆታ፣ የሃይማኖት እና የዘር) ወደ ሥራ መሠማራት፣
- በመደበኛ የሥራ ሰዓት በተቀባይ አገር ባለው/ የሠራተኛ ሕግ በተደነገገው መሠረት መስራት፤
- ለመደበኛ የቀን የሥራ ሰዓት የተመደበውን አነስተኛ የደመወዝ መጠን እና ትክክለኛውን የትርፍ ሰዓት ክፍያ የማግኘት፣ ክፍያውም በተቀባይ/ በመድረሻ አገር ከተወሰነው ትክክለኛ አነስተኛ የደመወዝ መጠን ማነስ የለበትም ወይም በሁለቱ አገሮች የሁለትዮሽ የሥራ ስምሪት የስምምነት ሠነድ ውስጥ ከተወሰነው አነስተኛ የደመወዝ መጠን ወይም በሁለቱ አገሮች በተፈረሙ ዓለም አቀፍ ሕጎች ከሁሉ የተሸለውን ክፍያ ማግኘት፣
- የዓመትና የሣምንት ዕረፍት በተቀባይ አገር ባለው የሠራተኛ ሕግ በተደነገገው መሠረት ፤ ነፃ ህክምና፣ ንፅህናው የጠበቀ መኝታ፣ የህይወትና አካል ጉዳት ኢንሹራንስ ሽፋን ማግኘት፤
- በዕረፍት ጊዜ ከሥራ ቦታ ያለመገኘት፤



- በመደበኛነት ከቤተሰብ ጋር (ቢያንስ በሣምንት አንድ ጊዜ) በስልክ ወይም በሌላ መንገድ በራሱ/ሷ ወይም በአሠሪው ወጪ (በተደረገው ስምምት መሠረት) መገናኘት፣
- ሠራተኛው በጥሩ ሥነ-ምግባር ካልተያዘ/ች ወይም የመብት ጥሰት ከተፈፀመበት/ባት (ቁጣ/ስሜታዊ፣ አካላዊና የወሲብ ትንኮሳ) በተቀባይ አገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ኤጀንቱን ማግኘት/ ማሳወቅ ፣
- የራሱን/የራሷን ሃይማኖት ከማክበር ጎን ለጎን የሌሎችን ሃይማኖት፣ ልምድና ባህል ማክበር፤
- በሥራ ውሉ የተገለፀው የሥራ ሁኔታ አንድም ቢጣስ ቅሬታ/አቤቱታ ማቅረብ/ማመልከት፤
- ምቹ የሥራና የመኖሪያ ቦታ መሟላት፣
- ፓስፖርት፣ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታና በራስ ምርጫ ሁል ጊዜ እንዲቀመጥ ማድረግ፣
- ከአያያዝ ጉድለት ወይም በግድየለሽነት ባሕሪ ካልሆነ በስተቀር በሥራና በአገልግሎት አሰጣጥ ጊዜ ለተሠበሩ ዕቃዎች ክፍያ መፈፀም አያስፈልግም፤

## በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ የቤት ውስጥ ሠራተኞች ግዴታ፣

በውጭ አገር ለሥራ የተሰማሩ የቤት ውስጥ ሠራተኞች ግዴታ የሚከተሉት ናቸው፡-

### ከጉዞ በፊት ኢትዮጵያ እያሉ፡-

- በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 መሰረት የሚከተሉት ወጪዎች ለሥራ ወደ ውጭ አገር በሚሄዱ ሠራተኞች ይሸፍናሉ፣
  - የፓስፖርት ማውጫ ወጪ፤
  - ከውጭ አገር የሚላክ የሥራ ቅጥር ውል ሠነድና ከወንጀል ነፃ ማስረጃ ሰርተፊኬት ማረጋገጫ ጋር የተያያዙ ወጪዎች፣
  - የሕክምና ምርመራ ወጪ፣ የክትባት ወጪ፣ የልደት ሠርተፍኬት ማስወጫ ወጪ እና፣
  - የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ወጪ፣




- በህጋዊ የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በኩል ወደ ውጭ አገር ለሥራ ይሂዱ፣ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸውን የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎችን አድራሻ/መረጃ ከሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ይውሰዱ፣
- የአዋጅ ቁጥር 923/2008 የሚጠይቃቸውን መስፈርቶች በማሟላት ሕጋዊ የውጭ አገር ሥራ ስምሪትን ይጠቀሙ፣ በዚሁ መሠረት በውጭ አገር ለሥራ የሚሰማሩ የቤት ውስጥ ሠራተኞች፡-
    - 18 ዓመትና ከዚያም በላይ መሆን አለባቸው፣
    - ቢያንስ የስምንተኛ ክፍልን ትምህርት ያጠናቀቁ፣
    - በሚሄድበት ሙያ ሠልጥነው የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት የወሰዱ፣
    - ቅድመ-ሥራ ስምሪትና እና የቅድመ- ጉዞ ሥልጠና/ገለፃ የወሰዱ፣
    - ከማይግራንት መረጃ ማዕከል፣ ከሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ስለመብትና ግዴታ መረጃ መጠየቅና ማግኘት የቅድመ ጉዞ ሥልጠና ገለፃ መውሰድ፣
- ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሄዱ ዜጎችን የጤና ሁኔታ ምርመራ እንዲያደርጉ በኢትዮጵያ መንግስት በተመረጡ የጤና ተቋማት በመመርመር የጤና ምርመራ ሠርተፍኬት መያዝ፣

## በተቀባይ አገር ሲደርሱና ወደ ሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ፣

- ተቀባይነትን ባገኙ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ማዕቀፍ ገደብ ውስጥ የተካተቱትን የአሰሪውን፣ የቤተሰቡን እና የአኗኗር ልምዳቸውን/ዘይቤአቸውን በቀላሉ መላመድ፣
- ሁልጊዜ ከቤት ከመውጣትዎ በፊት ለአሠሪዎ ማሳወቅና የመታወቂያ ወረቀት መያዝ፣
- የሚሠሩበትን አገር ሕግ፣ ማኅበራዊ ልምዶች፣ እንዲሁም ሃይማኖት፣ የባሕልና የሞራል ዕሴቶችን ተቀባይነትን ያገኙ ዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶችን እስካልጣሰ ድረስ ማክበር፣
- በሥራ ውሉ ውስጥ የተጠቀሱና የተስማሙበትን ሥራዎች በማክበርና በታማኝነት መሥራት፣
- የአሰሪዎንና የቤተሰቡን፣እንዲሁም በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችንና የእንግዶችን ሚስጥር እንዲሁም ገንዘብና ንብረት በታማኝነት መጠበቅ፣
- ሁል ጊዜ በጥሩ ሥነ-ምግባር መሥራት፣
- ሕግንና የሥራ ውሉን በመጣስ የሱን/የእሷን ሕይወት/ገንዘብ ወይም የሦስተኛ ወገንን ሕይወትና ገንዘብ አደጋ ላይ የሚጥል እስካልሆነ ድረስ የአሠሪውን ትዕዛዝና መመሪያዎች በጥሩ ሥነ-ምግባር ማክበርና መከተል፣



- ለሥራ መገልገያ የተሰጡ መሣሪያዎችን በጥንቃቄ መያዝና እንደ ባህሪያቸው መጠቀም፣ ሥራዎን ከጨረሱ በኋላ ለአሰሪው ማስረከብ፣
- የአገሩን ሕግ ወይም መመሪያና የተቀመጡ አስገዳጅ አሠራሮችን በሚጥስ መልኩ በክፍያም ሆነ በነፃ ለሌላ አሠሪ አለመሥራት፣
- የአሰሪውን የእሷንና የእሱን ቤተሰብ እና አብረው የሚኖሩ ሰዎችን ማክበርና መንከባከብ፣ በማንኛውም መንገድ ጉዳት ከማድረስ መቆጠብ፣
- በሥራ ውሉ በተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎች መሠረት የሥራ ውሉን ማቋረጥ፣
- ወደ አገርዎ ለዕረፍት መጥተው ወደ ቀድሞ አሰሪዎ የሚመለሱ ከሆነ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉትን ሰነዶች በመያዝ ቀርበው ሪፖርት በማድረግ ይመዝገቡ፣
  - ወቅታዊ ፓስፖርት፣
  - ለሥራ ወደሚሄዱበት አገር እንዲገቡ የተፈቀደበት ወቅታዊ ቪዛና የሥራ ፈቃድ ሰነድ እና
  - እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች መረጃዎች፣





## 2. በተደራሽ አገሮች የሚገኙ አሠሪዎች መብትና ግዴታ፣

### የአሰሪዎች መብት

አሰሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሉባቸው፣

- ሠራተኛው/ዋ ሕጎችን በመጣስ ከሥራ ቦታ ከቀሩ፣ ከጠፉና ግዴታቸውን ካልተወጡ አሠሪው የሥራ ውሉን ሊያቋርጥ/ሊሰርዝ ይችላል፡፡

### የአሠሪዎች ግዴታ

አሰሪዎች የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፣

#### ከጉዞ በፊት ሠራተኛው/ዋ ኢትዮጵያ እያለ/ች

- የሠራተኛውን/ዋን የደርሶ መልስ የትራንስፖርት ወጪ፣ የሥራና የመኖሪያ ፈቃድ፣ የኢንሹራንስ ሽፋንና ከቪዛ ጋር የተያያዘ ወጪዎችን፣ እንዲሁም የመግቢያ ቪዛ፣ ሰነድ ማረጋገጫ፣ የሥራ ውል ማፅደቂያና የአገልግሎት ክፍያ ወጪዎችን ይሸፍናል፣
- ለሠራተኛው/ዋ የህይወትና የአካል ጉዳት ኢንሹራንስ ሽፋን ይገባል፣

- የቤት ውስጥ ሠራተኞችን ከፍላጎታቸው ውጪና በሥራ ውሉ ከተጠቀሱት ሥራዎች ባሻገር ሌላ ሥራ እንዲሠሩ አለማስገደድ፣
- ሁልጊዜ በጥሩ ሥነ-ምግባር ሊመራ ይገባል፣

ሠራተኛው/ዋ ለሥራ ወደ ሚሄዱበት አገር ሲደርሱና ወደ ሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ፡-

- ምግብ፣ መጠጥ፣ የጤና ምርመራና መድሐኒት ማቅረብ ይኖርበታል፣
- የሞት አደጋ ሲያጋጥም የሟችን አስክሬን ወጪውን ሸፍኖ የግል ንብረቱንና ሳይከፈል የቀረ ደመወዝ ጭምር ወደ አገር ቤት መላክ፣
- የሠራተኛውን /ዋን የግል ሁኔታ ባከበረ መልኩ ምቹ የመኖሪያና የሥራ ቦታ ማዘጋጀት፣
- ሠራተኛዋ/ው በመድረሻ አገር አሰሪው ቤት ሲደርሱ አጠቃላይ ገለፃ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ገለፃውም የቤት ውስጥ ጉብኝት፣ የዕቃዎችን (መሣሪያዎችን) አጠቃቀምና የቤቱን ህግ ማሳወቅ ሲሆን በዚህ ብቻ ሳይወሰን ሌሎችንም ይጨምራል፡፡
- ለሠራተኛው/ዋ የሥራ ውሉ ያካተታቸውን የሥራ ሁኔታዎች ማስረዳትና በግልፅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ፤
- ለሠራተኛው/ዋ የመኖሪያ ፈቃድና የሥራ ቪዛ ማውጣትና ማደስ፣



- ሠራተኛውን/ዋን የሚጎዱ ድርጊቶች፣ ብዝበዛ፣ ትንኮሳንና ማንጓጠጥን መከላከል/አለማድረግ፣
- የሠራተኞችን ክብርና ደህንነት መጠበቅና መከላከል፣ ዋስትናም መስጠት፣
- የቤት ውስጥ ሠራተኞችን አካልና ሞራል የሚጎዱ ወይም ጤናቸውንና ህይወታቸውን ለአደጋ የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን አለማድረግ፣
- የሠራተኛውን/ዋን የዕረፍት ጊዜ ማክበር፣ በቅድሚያ ትርፍ ሥራውን ለመስራትና በሌላ ቀን ዕረፍት እንደሚሰጥ ሁለቱ ወገኖች እስካልተስማሙ ድረስ በዕረፍት ጊዜያቸው ወይንም በሣምንት ዕረፍታቸው እንዲሰሩ አለመጠየቅ፣ ፣
- የሠራተኛውን/ዋን ደመወዝ በስምምነቱ መሠረት በወሩ መጨረሻ ወይም ወር በገባ በሦስተኛው ቀን መክፈል፣
- ሥራና ሠራተኛን ለማገናኘት የወጣ ወጪን ለተመተካት ሲባል ከሠራተኛ ደመወዝ ላይ ምንም ዓይነት ክፍያ፣ ወጪዎች ወይም ኮሚሽን መቀነስ የለበትም፣






## 3. የውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ኃላፊነት፣

የውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ግዴታ፡-

### ከጉዞ በፊት ሠራተኛው/ዋ ኢትዮጵያ እያለ/ች

- ለሥራ ወደ ውጭ አገር ከሚሄዱ ዜጎች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሙሉ ለሙሉም ሆነ በግማሽ ምንም ዓይነት ወጪዎችን ወይም ተዛማጅ ክፍያዎችን መቁረጥ/መቀነስ የለባቸውም፣
- ለውጭ አገር ሥራ ስምሪት የሚደረግ የሠራተኛ ምልመላ ግልፅና ክፍት በሆነ መንገድ ማስታወቂያ ወጥቶ መሆን አለበት፡፡
- አጠቃላይ የሥራውን፣ የተቀባይ አገርን ሁኔታና የቅድመ ጉዞ ገለፃና የምክር አገልግሎት ወደ ውጫ አገር ለሥራ ለሚሄዱ ዜጎች ገለፃ ማድረግ/መስጠት፣
- የውጭ አገር የሥራ ስምሪት የሥራ ውል ዜጎች በሚገባቸውና በሚረዱት ቋንቋ ተፅፎ ወይም ተተርጉሞ ቅጂው በውጭ አገር ሥራ ለሚሠማሩ ዜጎች መስጠት አለበት፣
- በሥራ ውሉ የተዘረዘሩትን የሥራ ሁኔታዎች በውጭ አገር ሥራ ለሚሰማሩ ሠራተኞች ማስረዳት፣

- ደረጃውን የጠበቀና መርሆን የተከተለ ትክክለኛ የሠራተኛ ምልመላ በማድረግ በውጭ አገር ለሥራ የሚሠማሩ ዜጎችን በምልመላ፣ በሥራ ስምሪትና በሚመለሱበት ጊዜ ከሚደርስ ማንኛውም ብዝበዛና ትንኮሳና፣ ማንጓጠጥ መከላከል፣

## ሠራተኛው/ዋ ለሥራ ወደ ሚሄዱበት አገር ሲደርሱና ወደ ሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ፡-

- ሠራተኞች በሚመለመሉበትና ወደ ሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ በዘር፣ በቀለም ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በመጡበት ማህበረሰብ ወይም በሌሎች መለያ መንገዶች ላይ ከተመሰረተ መድልዎ የፀዳ መሆን ያኖርበታል፣
- በመካከለኛው ምስራቅ አረብ አገራት የሚሠሩ ሠራተኞች ሲመለምሉና ወደ ሥራ ሲያሰማሩ ጥበቃ ማድረግ፣
- በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ተመልምለው ወደ ገልፍ አገሮችና ሊባነን የሚሄዱ ሠራተኞችን መመዝገብና አስፈላጊ መረጃዎችን በሙሉ መያዝ፣
- የሠራተኛው ውል በፀደቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሥራ ማሰማራት፣
- ወደ ውጭ አገር ሄደው ወደ ሥራ የተሰማሩ ዜጎችን መረጃ በ15 ቀን ውስጥ በመድረሻ አገር ላለው የኢትዮጵያ ኤንባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት በማሳወቅ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ይገባል፣
- በመድረሻ አገር ሠራተኞች የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- የሥራ ውሉ አለመቋረጡን ማረጋገጥ፣



## 4. የላኪና ተቀባይ አገሮች ኃላፊነት፣

### የመድረሻ አገሮች ሚናና ኃላፊነቶች

የመድረሻ አገሮች ኃላፊነቶች፣

- በሥራ ላይ ያሉ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞችና አሰሪዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት የተዘረጉ የአሰራር ስልቶች መኖራቸውንና ሠራተኛው ፍትሕን የሚያገኝበት ፍርድ ቤቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣
- በሥራ ላይ ያሉ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ ተቀመጡ ሕጎችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ በተጨማሪም የሠራተኛውን የሥራና የኑሮ ሁኔታዎች ከሥራ ውሉና ከሁለትዮሽ ስምምነቱ ጋር መጣጣማቸውን በመደበኛ ቁጥጥር ማረጋገጥ፣
- የመድረሻ አገር ዜጎችና በሥራ ላይ ያሉ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞችን በዕኩልነት ማየት፣

- በሥራ ላይ ያሉ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች የመብት ጥሰት ሲያጋጥማቸው የሚታይበትና የሚፈታበት አሰራርና ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣
- በሥራ ላይ ያሉ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞችን ሰብዓዊና የሥራ ላይ መብቶች ጥበቃን በተመለከተ በብቃት ማራመድ፣
- በሥራ ላይ ያሉ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች ለሚያጋጥማቸው የመብት መጣስና ትንኮሳን መከላከል፣ አስፈላጊውንና ትክክለኛውን ጥበቃና ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

## የኢትዮጵያ መንግስት ሚናና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ መንግስት/ሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት፡-

- በሥራ ውሉ የተካተቱ የሥራ ሁኔታዎች በሁለቱ አገሮች የሁለትዮሽ የሥራ ስምምነትና በሁለቱ አገሮች ባሉ የሕግ አግባቦች መሰረት መፈፀማቸውን ማረጋገጥ፣
- ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሄዱ ዜጎች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት የሥራ ውላቸውን ቅጂ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሄዱ ዜጎች የሥራ ውሉን ይዘትና የሥራ ሁኔታውን ሙሉ በሙሉ በግልፅ መረዳታቸውን ማረጋገጥ፣
- የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ወደውጭ አገር ለሥራ የሚሄዱ ዜጎችን እንዲመለምሉ ፈቃድ መስጠት፣
- የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች በሚልኳቸው ዜጎች ላይ የሚደርሰውን የህግ መጣስና ብዝበዛ የመከላከል ልምዳቸውን መቆጣጠርና መከታተል፣
- ወደ ውጭ አገር ለሥራ ለሚሄዱ ዜጎች በመደበኛነት የቅድመ-ሥራ ስምሪትና የቅድመ-ጉዞ ገለፃ /ሥልጠና በነፃ መስጠት፣
- በውጭ አገር መሥራት ለሚፈልጉ ዜጎች ስለ ውጭ አገር ሥራ ስምሪት ሂደትና በውጭ አገር ያለውን የሥራ ሁኔታ አስመልክቶ መረጃና ድጋፍ መስጠጥ፣

- በውጭ አገር በሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች ደህንነት፣ መብት እና ክብር መጠበቁን መከታተልና ማረጋገጥ፣
- በውጭ አገር የሚሠሩ ሠራተኞች አቤቱታ መቀበያ ስልት መቀየስና ከተቻለ አቤቱታው በስምምነት እንዲፈታ፣ ካልሆነ በመድረሻ አገሮች ያለውን መደበኛ ህግና ሥርዓት ተከትሎ እንዲፈታ ማድረግ መቻል፣

## For further information, please contact:

**Aida Awel (Ms)**

Program Manager,

ILO Country Office for Djibouti, Ethiopia, Somalia,
South Sudan and Sudan

Menelik II Avenue, ECA Congo Building, 5th Floor

P.O Box 2788, Addis Ababa, Ethiopia

Email:aida@ilo.org

ይህ  የግንዛቤ ማስጨበጫ/ የመረጃ ብሮሸር/መፅሐፍ የአሳታሚውንና
የፀሃፊውን አስተያየት የሚገልፅ ሠነድ/ብሮሸር አይደለም፡፡

ይህ የመረጃ መፅሐፍ እ.አ.አ አፕሪል 2019 ዓ/ም በዓለም ሥራ ድርጅት
የተዘጋጀ ነው፡፡

በዓለም ሥራ ድርጅት የተዘጋጀ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት መረጃ




UKaid
from the British people